# በስኬቶች የታጀበ ቃል ኪዳን  ልደት

ክፍል ሁለት

ኢ.ብሳ ነመራ 12-3-14

በዚሁ ርዕስ በቀረበ ክፍለ አንድ ፅሁፍ በዘውዳዊውና ወታደራዊው የመንግስት ስርአቶች የነበረውን ብሄራዊና ኢኮኖሚያዊ ጨቆናና ጭቆናው የወለደውን ትግል እስከ የደርግ ውድቀት ድረስ ያለውን ሁኔታ በአጭሩ ተመልክተናል። ከህገመንግስቱ መፅደቅ እስከ አሁን የህገመንግስቱ 20ኛ ዓመት ድረስ ያለውን ሁኔታ ደግሞ በዚህ በክፍል ሁለት ፅሁፍ እንመለከታለን።

የመጨረሻው የኢትዮጵያ አምባገነን የመንግስት ሥረአት የነበረው ወታደራዊው ደርግ መገርሰሱን ተከትሎ፣ በሃገሪቱ ከዚያ ቀደም የነበረውን በህዝቦች መሃከል የነበረ ጭቆናና ጭቆናው ያስከተለውን የተዛባ ግንኙነት የሚሽር አዲስ የመንግሥት ሥርአት መገንባት አስፈላጊ ሆነ። በመሆኑም የደርግን መንግስት በትጥቅና በተለያየ መንገድ ሲታገሉ የነበሩ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት የነበሩ ሁሉም ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ለመወሰን በአንድ አዳራሽ ታደሙ።

የኢትዮጵያ መፃኢ ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ከታደሙት መሃከል ከሃያ በላይ የሚሆኑት የብሄራዊ ነፃነት ግንባሮች ነበሩ። ወታደራዊው ደርግ እንዲወድቅ በማደረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸውም እነዚህ የትጥቅ ትግል ያካሄዱ ብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች ነበሩ። እነዚህ የነፃነት ግንባሮች ባካሄዱት መራራ ትግል የወታደራዊውን ደርግ መንግስት ከስሩ ነቅለው ካስወገዱ በኋላ፣ የየራሳቸውን ነፃ መንግስት የመመስረት ዕድል በእጃቸው የነበረ ቢሆንም፣ ይህን ከማድረግ ይልቅ አብረው መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ ማደላደል ነበር የመረጡት። የዚህ አቋማቸው መነሻ "ተገንጥሎ ነፃ መንግስት መመስረት በራሱ ብሄራዊ ጭቆና ወደሌለበት ሥርአት የሚወስድ ብቸኛው አማራጭ ሳይሆን፣ የመጨረሻው አማራጭ ነው" የሚል እመነት ነበር።

እናም ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካና የነፃነት ትግል መሰረት የሆነው ብሄራዊ ጭቆና የሌለበትንና በእኩልነት መኖር የሚችሉበትን ሥርአት ለመመስረት ተስማሙ። በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ተሰባስበው የደርግን ሥርአት ለመጣል ባበረከቱት አስተዋፅኦና በሚወከሉት ሕዝብ ቁጥር ልክ ሥልጣን የተጋሩበት የሽግግር መንግስት መሰረቱ።

የዚህ የሽግግር መንግስት ቀዳሚ ዓላማ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በመቻቻልና በመከባበር ላይ በተመሰረተ አንድነት  የሚኖሩበትን የመንግስት ሥርአት መመሥረት ነበር። ይህ መንግስት የሚመራበትን ህገመንግስት መቅረፅ የዚህ የሽግግር መንግሥት ዋና ተልዕኮ ነበር።

በዚህ መሰረት ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም በሌሎች አመለካከቶች የተደራጁ ፓርቲዎች የተወከሉበት የህገመንግስት አርቃቂ ኮምሽን ተቋቋመ። ይህ ኮምሽን የመጀመሪያውን የህገመንግሥት ረቂቅ አዘጋጀ። ረቂቁን ኮምሽኑ ራሱ ወይም ከፍተኛው የስልጣን አካል የሆነው የሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት እንዲያፀድቀው አልተደረገም። ከዚህ ይልቅ የህገመንግስቱ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያፀድቀው ነበር የተደረገው።

በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የሚወከሉ ሁሉም ለአካለ መጠን የበቁ ኢትዮጵያውያን በረቂቅ ህገመንግስቱ ላይ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲወያዩ ተደረገ። በዚህ ውይይት፣ መቀነስ አለበት ያሉትን ቀንሰው፣ መጨመር አለበት ያሉትን አክለው ረቂቁን በማዳበር መልሰው ላኩት። ኮምሽኑ በህዝብ ዳብሮ የተላከለትን ረቂቅ አሻሽሎ ሕዝብ ለሁለተኛ ግዜ እንዲወያየበት ወደ ሕዝብ መራው። ረቂቁ ለሁለተኛ ግዜ የተመራለት የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደመጀመሪያው አንቀፅ በአንቀፅ አድቅቆ ተወያይቶ ማሻሻያ ሃሳቦችን አካቶ ላከው።

ከዚህ በኋላ ይህ ሁለት ግዜ በህዝብ ውይይት የዳበረ ረቂቅ ሕገመንግሥት ወደመፅደቅ ሂደት ተሸጋገረ። የፀደቀው በአርቃቂ ኮምሽኑ ወይም በሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት አልነበረም። በሕዝብ ነበር የፀደቀው። ህዝብ በመረጣቸው ተወካዮች።

ሁሉም በሕገመንግስቱ ላይ የተወያዩ የተለያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አባላት የሆኑ ለአካለ መጠን የደረሱ ኢትዮጵያውያን በምስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሥርአት የህገመንግስት አፅዳቂ ጉባኤ አባላትን መረጡ። ምርጫው የተለያየ አመለካከት ያላቸው ወገኖች የተሳተፉበት፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ነበር። በዚህ ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የተመረጡ አባላትን የያዘው የህግመንግስት አፅዳቂ ጉባኤ ሁለት ግዜ በሕዝብ ውይይት የዳበረውን ረቂቅ ሕገመንግስት እያንዳንዷን አንቀፅ በድምፅ ብልጫ እያሳለፈ በመጨረሻ ሙሉውን ህገመንግስት አፀደቁ።

የዚህ ህገመንግስት ባለቤቶች፣ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ እርስ በእርስ በመከባበርና በመቻቻል በእኩልነት የሚኖሩበትን የመንግስት ሥርአት መመስረት የቻሉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ናቸው። የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ በእኩልነት ለመኖር የተስማሙበት የቃልኪዳን ሰነድ ነው።

ይህ በህገመንግስቱ መግቢያ ላይ በግልፅ ተቀምጧል። የህገመንግስቱ መግቢያ በብዙዎች የሚታወቅና በተለያየ አጋጣሚዎች የተጠቀሰ ቢሆንም፣ መሰረታዊ በመሆኑ በዚህ ፅሁፍ ላይ ልጠቅሰው ወድጃለሁ። የሥግመንግስቱ መግቢያ፤

*እኛ የኢትዮጵያ በሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች፤*

*በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን እድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ ፍላጎታችን በሕግ የበላይነትና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤*

*ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሄር/ብሄረሰብ መሰረታዊ መበቶች መከበራቸው፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ፅኑ እምነታችን በመሆኑ፤*

*ኢትዮጵያ ሃገራችን የየራሳችን አኩሪ ባህል ያለን፣ የየራሳችን መልከዓምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንበትና የምንኖርበት ሃገር በመሆኗ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤*

*መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤*

*ጥቅማችንን፣ መብታችንንና ነፃነታችንን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት አስፈላጊነትን በማመን፤*

*በትግላችን በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሠላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ፤*

*ይህ ህገመንግስት ከዚህ በላይ ለገለፅናቸው ዓላማዎችና እምነቶች መሳሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን በህገመንግስት ጉባኤ አፅድቀነዋል።*
ይላል።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ የሆነው የኢፌዴሪ ሕገመንግስት መሰረታዊ መርሆቹንም አስፍሯል፤ በሕገመንግሥቱ ምዕራፍ ሁለት ላይ። በዚህ ምዕራፍ ከአንቀፅ 8 እሰከ 12 የሰፈሩት የሕዝብ ሉዓላዊነት፤ የህገመንግስት የበላይነት፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፤ የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት፤ የመንግሥት አሰራርና ተጠያቂነት መርሆችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሰፍረዋል። ከእነዚህ የህገመንግሥቱ መርሆች ድንጋጌዎቸ መሃከል፣ የህዝብ ሉዓላዊነትን የሚመለከተውን እጠቅሰዋለሁ።

በአንቀፅ 8 "የሕዝብ ሉዓላዊነት" በሚለው ርዕሥ ሥር፤

- *የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የኢትዮጵያ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።*
- *ይህ ሕገመንግሥት የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ነው።*
- *ሉዓላዊነታቸውም የሚገለፀው በዚህ ሕገመንግሥት መሰረት በሚመረጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳተፎ አማካይነት ይሆናል።*

ይላል።

የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀፅ 39 “የብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት” በሚል ርዕሥ ሥር የሚከተለውን ደንግጓል፤

- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እሰከመገንጠል ያለው መብቱ በማንኛውመ መልኩ የተጠበቀ ነው።*
- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ የማዳብርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው።*
- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት በሄሩ፣ ብሄረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በውክልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።*

እንግዲህ ይህ በህዝብ ተዘጋጅቶ በህዝብ የፀደቀ የኢዮጵያ ብሄሮች፣ ብሀረሰቦችና ሕዝቦችን መብትና ነፃነት፣ የህግ የበላይነት ያረጋገጠ ህገመንግስት የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች  የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ ፀደቆ ሰራ ላይ ከዋለ አነሆ 20 ዓመት ሞላው፤ ህዳር 29፣ 2007 ዓም ላይ።

ህገመንግስቱ በስራ ላይ በዋለባቸው ያለፉ ሃያ ዓመታት ድንጋጌዎቹ ትግባራዊ ተደረገዋል። ከእነዚህ ድንጋጌዎቸ የሚፈለገው የመብትና ነፃነት መከበር፣ የዴሞክራሲ መሰፈን፣ በልማት የተሻለ ህይወት መኖር . . . ዕውን ሆነዋል።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ስልጣን በውክልና በሰጧቸው ሰዎቸ ብቻ የመተዳደር፣ ፍትህን ጨምሮ የመንግስት አገልግሎት በቋንቋቸው የማገኘት፣ በቋነቃቸው የመተዳደር፣ ለጆቻቸውን በቋንቋቸው የማስተማር መብታቸው ተከብሮላቸዋል።

ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋቸውንና  ባህላቸውን እያጎለበቱ፣ ታሪካቸውን እየተንከባከቡ የገኛሉ። በአሁኑ ገዜ የኦሮሚኛ፣ የሲዳምኛ፣ የሶማሊኛ፣ የትግርኛ ቋነቋዎች በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እየተሰጡ ይገኛል። በተለይ ኦሮሚኛ እሰከ ፒ ኤች ዲ ዲግሪ ድረሰ እየተሰጠ ነው። ይህ ቋነቋው ላይ ጥናቶችን በማካሄድ፣ ቋንቋውን የስነፅሁፍ፣ የፍልስፍናና የሳይንስ ቋንቋ ማድረግ ያስችላል። ቋንቋን የማዳበር መብት ተግባራዊነት ይህን ይመስላል።

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላቸውንም እያጎለበቱ ነው። በየክልላቸው የባህል ማዕከላት በመገንባት ነባር ባህላቸው በቅርስነት እንዲጠበቅ፣ አንዳንዶቹንም በዓለም አቀፍ የሰው ልጅ ቅርስነት እንዲመዘገበ እያደረጉ የገኛሉ። ባህላቸውን አንዱ ለሌላው እያስተዋወቁ እየተደናነቁና እሴት እየተጋሩ በጋራ የሚደምቁበትን ሁኔታ እየፈጠሩ ነው። የብሄሮችንና ብሄረሰቦችን ማንነት ለመድፈቀና ለማጥፋት የተቀነባበረውን የፈጠራ ታሪካቸውን እያሰተካከሉና አየተነከባከቡም የገኛሉ።

በብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች መሃከል ተፈጥሮ የነበረው አንዱ ምርጥ ኢትዮጵያዊ፣ ሌሎች ደግሞ ምራጭ ተደርገው እንዲወሰዱ ያደረገው አመለካከት ጥቂት የቀደሞው ስረአቶች ርዝራዦች ጋር ካልሆነ አየጠፋ ነው። አሁን ብሄሮቸና በሄረሰቦች በህገመንስቱ መሰረት በፍቃዳቸው በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ የህዝቦች አንድነት ለመመሰረት በገቡት ቃለ ኪዳነ መሰረት ሁሉመ እኩለ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

ይህ ሁኔታ የትልቅና ትንሽ ኢትዮጸያዊነት አመለካከትን አሰቀርቷል። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ለሚኖሩበት መሬትና መሬቱ ላይ ለሚገኝ የተፈጥሮ ሃብት ተበሎ በኢትዮጵያ ውስጥ የተጠቃለሉበት የወሰን እንጂ የህዝብ አንድነት የሌላት ሃገር አይደለችም። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው

እያስተዳደሩ እርስ በርስ በመከባበር በፌደራላዊ ስርአት አብረው ለመኖር የተስማሙባት የህዝቦች አንድነት ያላት ሃገር ነች።

እርግጥ አሁንም በህገመንግስቱ የተረጋገጠው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ያልተዋጠላቸው ያሮጌው ስርአት ርዝራዥች አሉ። እነዚህ ወገኖች በህገመንግስቱ አንቀፅ 39 ንኡስ አንቀፅ 1 ላይ *"ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማንኛውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው።"* በሚል የተረጋገጠውን መብት "የወሰን አንድነት ያናጋል፣ ሃገር ያፈርሳል . . ." እያሉ በማላዘን ላይ የገኛሉ።

በሕገመንግስቱ ላይ የተደነገገው እስከመገንጠል የዘለቀ መብት ግን፣ አዲሲቱን ኢትዮጵያ በፍቃዳቸው የገነቡት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነታቸው ሳይሸራረፍ የሚከበር ለመሆኑ የተሰጠ ዋስትና እንጂ መገንጠልን የሚያነሳሳ አይደለም። ተገንጥሎ ነፃ መንግስት መመስረት መድረሻ አይደለም። መገንጠል መብትና ነፃነት ወደተከበረበት ስርአት የሚወስድ አንድና የመጨረሻ አማራጭ ነው። የኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ይህን ያውቃሉ። በመሆኑም መብትና ነፃነቶቻቸው ከተከበሩ ከሌሎች ጋር በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ኖሯቸው መኖርን ይመርጣሉ። እስከመገንጠል የሚዘልቀው መብት፣ መብትና ነፃነታቸው ለመከበሩ ዋስትና ነው። "መብትና ነፃነታችን አልተከበረም" ብለው ሲያምኑ ጥያቄው የብሄሩ ወይም የብሄረሰቡ ሕዝብ መሆኑን በሚያረጋግጥ ስረአት የሚገነጠሉበት አካሄድ ነው።

አንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ የመገንጠል ጥያቄ የሚያነሳው የመገንጠል መብት በህገመንግስት ስለተደነገገ ሳይሆን በሄራዊ ጨቆና ሲኖረበት ብቻ ነው። ጭቆናው እስካለ ድረስ የመገነጠል መብት በህገመንግስት መደንገጉ ወይም አለመደንገጉ ጥያቄውን ከመነሳት አይገድበውም። እናም በዚህ ላይ ያለው ስጋት "የተወሰኑ ብሄሮች/ብሄረሰቦች ከሌላው ያነሰ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ሰላላቸው፣ መሬቱንና የተፈጥሮ ሃብቱን የዘው ሊሄዱ ይችላሉ" ከሚል የተዛባ ግንዛቤ የመነጨ ነው። አሁን ሁሉም የኢትዮጵያ በሄሮች - "የኢትዮጵያዊነት ሰሜታቸው ቀዝቃዛ ነው" ሲባሉ የነበሩ የሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ብሄሮች ጭምር መብትና ነፃነታቸውን ያረጋገጠችላቸው ኢትዮጵያ

ዜጎች መሆናቸውን ተቀብለዋል። መብትና ነፃነታቸው እስከተከበረ ድረስ ኢትዮጵያዊነታቸው ይቀጥላል። የአንድ ብሄር የመገንጠል ወይም ያለመገነጠል ጥያቄ፤ የመብትና ነፃነት መከበር ወይም ያለመከበር ጉዳይ ነው፤ በቃ።

የኢትዮጵያ ብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን ብሄራዊ መብትና ነፃነትን ደፍጥጠው የነበሩት ዘውዳዊና ወታደራዊ የመንግስት ስርአቶች በርካታ ብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች እንዲፈጠሩ የሚያስገድድ ሁኔታን ፈጥረው ነበር። ይህ ሁኔታ በአንድ ወገን ብሄራዊ ነፃነት ግንባሮች ለነፃነት የሚያካሂዱት ትግል፣ በሌላ ወገን አምባገነኖቹ በተለይ የወታደራዊው መንግስት በየአቅጣጫው የተቀሰቀሰውን የነፃነት ጥያቄን ለማፈን የወጀው ጦርነት ሃገሪቱን የጦር አውድማ አድርጓት ነበር። ይህ ሁኔታ እጅግ በተባባሰበት የደርግ ስርአት “ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር !” የሚለው መፈክር የስርአቱ መገለጫ ለመሆን በቅቶ ነበር።

ብሄራዊ የነፃነት ግንባሮች የደርግን ስርአት አስወግደው ነፃነታቸውን ካወጁና ይህን ነፃነታቸውን በኢፌዴሪ ህገመንግስት አረጋግጠው በመቻቻልና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት ኖሯቸው ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከጀመሩ በኋላ በሃገሪቱ ፍፁም ሰላም ሰፍኗል። ኢትዮጵያ የራስዋን ሰላም ከማረጋገጥ አልፋ ዘላቂ የሰላም ዋስትና እንዲኖራት በምስራቅ አፈሪካን ሰላም በማስከበር ቀንዲል ለመሆን በቅታለች። አሁን በሃገሪቱ ፍፁም ሰላም ሰፍኗል። የጦርነት ስጋትም ተወግዷል።

ይህ ሁኔታ በወታደራዊ ደረግ የመንግስት ስርአት “ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር !” በሚል መፈክር የመንግስት ትኩረቱ ሁሉ ብሄራዊ የነፃነት ንቅናቄዎችን ማፈን ላይ በመሆኑ ኢኮኖሚው ክፉኛ ተጎዶቶ ነበር። አርሶ አደሩ ምንም አይነት ምርታማነቱን የሚያሳድግ ድጋፍ ስለማይደረግለት አርሶ አደሩ ያመርት የነበረው ራሱን መመገብ እንኳን የማያስችለው እጅግ አነስተኛ ምርት ነበር። ይህ ሁኔታ “ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር !” መፈክር መሰረት አርሶ አደሩ የእርሻ ስራውን ትቶ በግዳጅ ወደ ጦርነት ይጋዝ ስለነበረ መታረስ የሚገባው መሬት ጦም በማደሩ ወትሮም ዝቅተኛ የነበረው የሃገሪቱ የምርት መጠን የባሰ አሽቆልቁሎ ነበር።

ወታደራዊው መንግስት በጀቱን በሙሉ ከውጭ የሚገኝ ብድርን ጭምር የጦርነት ወጪውን ለመሸፈን ስለሚያውለው፤ የመሰረተ ልማት፣ የማምረቻና የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ማቋቋሚያ ወይም ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት አይደረግም ነበር። የግል ኢነቨስትመንትም፤ ስርአቱ በሚከተለው የዕዝ ኢኮኖሚ ምክንያት የተከለከለ በመሆኑ የኢንቨስትመንት አቅም ያላቸው ባለሃብቶች ባለመፈጠራቸው፣ እንዲሁም የውጭ ባለሃብቶችንም በተመለከተ ስርአቱ የሚከተለው ፖሊሲ ለኢንቨስትመንት ስለማይጋብዝና ሃገሪቱ የጦርነት ቀጠና በመሆኗ ኢነቨስተሮቸ ቢጋበዙ እነኳነ የመምጣት ፈላጎት ስለሌላቸው ኢኮኖሚው የኋሊት እየተንደረደረ ነበር። ይህ ሁኔታ በሃገሪቱ ስራአጥነትና ድህነት ስር ሰዶ እንዲንሰራፋ አድርጓል።

አሁን በሃገሪቱ ጦርነት የለም። በመላው ሃገሪቱ ሰላም ነግሷል። የኢፌዴሪ ሕገመንግስት የኢትዮጵያ ብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን መብትና ነፃነት እነዲከበር በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመገንባትና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ሰላም እነዲሰፍን ማድረግ አስችሏል። ይህ ሰላም፤ መንግስትና ህዝቡ ለዘመናት የኖረውንና ስር የሰደደ ድህነት ማስወገድ ላይ እነዲያተኩር ማድረግ አስችሏል። አሁን ሃገሪቱ የፀረ ድህነት ትግልና የብልፅግና ግስጋሴ ላይ ትገኛለች።

ሃገሪቱ ባለፉ አስር አመታት ያስመዘገበችው እድገት በተጨባጭ በህዝቡ ኑሮ ላይ የተገለፀ በመሆኑ እንዲሁም በመንግስታትና በዓለም አቀፈ የኢኮኖሚ ተቋማት የተመሰከረለተ በመሆኑ፣ በዚህ ዙሪያ በዙ ማውራት አያስፈልገኝም። በአጭሩ ግን ባለፉ አስር ዓመታት በተመዘገበ የኢኮኖሚ እድገት ኢትዮጵያ በምግብ ራስዋን ችላለች። አሁን አስከፊ ድርቅ ሃገሪቱን ቢመታ እንኳን በ1966 እና በ1976/77 እንደታየው አስከፊ ቸነፈር አይከሰትም። እርዳታ ከመደረሱ በፊት በራሷ የምግብ ክምችት የምግብ እጥረትን መቋቋም የሚያስችል ደረጃ ላይ ደርሳለች።

50 በመቶ የነበረው ከድህነት በታች የሚኖር ህዝብ መጠን ባለፉ አስር አመታት በተመዘገቡ የልማት ስኬቶች ከ29 በመቶ በታች አሽቆልቁሏል። ከ100 ዶላር የማይበልጥ የነበረው አመታዊ አማካይ የዜጎች የነብስ ወከፍ ገቢ 600 ዶላር ደረሷል። በግልና በመንግስት ፕሮጀክቶች የተፈጠረውን የስራ እድል ሳይጨምር በአነስተኛና ጥቃቅን

ተቋማት ባለፉ አምስት ዓመታት ለ6 ሚሊየን ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል። የዚህን እድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ ኢትዮጵያ በ2017 ዓ/ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ትሰለፋለች።

ኢትዮጵያ አሁን የድህነትና የረሃብ ምሳሌ መሆኗ ቀርቷል። በግብርናና በኢንደስትሪ ዘርፎች ባስመዘገበችው ስኬት የምትጠቀስና ተሞክሮዋን ለዓለም የምታካፍል ሃገር ለመሆን በቅታለች። በተለያየ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ ተሞክሮዋን እንድታካፍል እየተደረገ ነው።

በሃገሪቱ የተረጋገጠው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት፣ ዜጎች ስልጣን በውክልና የሚሰጡበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ የህግ የበላይነት፣ ሰላም፣ የህዝቡን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ ያሸጋገረ ልማት . . . የኢፌዴሪ ህገመንግስት ትሩፋቶቸ ናቸው። ዝንድሮ ከሚከበረው 9ኛው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በስኬት የታጀበው ህገመንግስታችን የፀደቀበትን 20 የድል በአልም እናከብራለን። እንኳን የሰላምና የልማት መሰረት ለሆነው ህገመንግስታችን 20ኛ ዓመትና የብሄር በሄረሰቦቸ ቀን በሰላም አደረሳችሁ።